SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

**ለ2019-20 የሁሉም ተማሪዎች የተማሪ የተጠቃሚ ስሞች(Username) ለውጥ**
**እና ለ 5 ኛ እና 6 ኛ ክፍል ገቢ ተማሪዎች የይለፍ ቃል(password) ለውጥ መረጃ**

## የተጠቃሚ ስም ለውጥ

የተማሪ የተጠቃሚ ስሞች በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተለያዩ የትምህርት ድርጣቢያዎች ለምሳሌ ስኩሎጂ ፣ ኦፊስ 365 ወዘተ እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል። ለ2019-20 የትምህርት ዓመት ፣ ምንም እንኳን ተማሪዎ ትምህርት ቤቶችን ቢቀይሩ  እስከ የመጨረሻ ምረቃ ድረስ የተጠቃሚ ስማቸው አንድ ዓይነት እንዲሆን ለማስቻል በተማሪው የተጠቃሚ ስም  ላይ ለውጥ ተደርጓል!  በእርግጥ ፣ ልጅዎ የስም ለውጥ ካደረጉ የተጠቃሚ ስማቸውን የመቀየር አማራጭ አላቸው።

**ተማሪዎች:** የተጠቃሚ ስምዎ የመጀመሪያ 4 ፊደላት በ 1 ይተካሉ ። አዲሱን የተጠቃሚ ስምዎን ማረጋገጥ ከፈለጉ፣ከነሐሴ 13 እስከ መስከረም 14፣ 2019 ድረስ ባለው ግዜ ውስጥ ወደ ሶርስ መግባት ይችላሉ። ሶርስን በ: http://ps.seattleschools.org መጎብኘት ይችላሉ።

**የድሮውን የተጠቃሚ ስም** አንዴ ካስገቡ በኋላ **አዲሱ የተጠቃሚ ስም** ይመጣልዎታል።

ለምሳሌ:  ስምዎ John Stanford Smith ከሆነ፣ የእርስዎ **የቀድሞ የተጠቃሚ ስም: XXX_jssmith** ይሆናል፣ እና አዲሱ **የተጠቃሚ ስምዎ** አሁን: **1jssmith** ይሆናል ማለት ነው።አዲሱን የተጠቃሚ ስምዎ ለማግኘት ችግር ከገጠምዎ ሁልጊዜ አስተማሪዎን ወይም የቤተ መጻህፍት ባለሙያን ማነጋገር ይችላሉ።

## ለ 5 ኛ እና 6 ኛ ክፍል ገቢ ተማሪዎች የይለፍ ቃል ለውጥ

ለ 2019-20 የትምህርት ዓመት እና ከዚያ በኋላ ወደ 5ኛ ክፍል የሚገቡ  ሁሉም **አዲስ** ተማሪዎች በ MMDD መልክ የነበረው የባለአራት የይለፍ ቃላቸው ወደ 8 ካረክተር ያለው የይለፍ ቃል መለወጥ አለባቸው።  ለዚህ የትምህርት ዓመት ብቻ (2019-2020) ፣ ወደ 6 ኛ ክፍል የሚገቡ ሁሉም ተማሪዎች ጭምር በ MMDD  መልክ የነበረው የባለአራት የይለፍ ቃላቸው ወደ 8 ካራክተር ያለው የይለፍ ቃል መለወጥ አለባቸው።  መጀመሪያ ለመግባት ሙሉ የልደት ቀናቸውን ይጠቀማሉ: MMDDYYYY::  ከገቡ በኋላ፣ወዲያውኑ ለአዲሱ የተጠቃሚ ስማቸው የሚጠቀሙበት  ቢያንስ 8 ካራክተር ርዝማኔ ያለው አዲስ የይለፍ ቃል እንዲመርጡ ይጠየቃሉ። አዲሱ የይለፍ ቃል ልዩ  ካራክተሮች ሊኖሩት ይችላሉ። ሆኖም ግን የድሮውን10 የይለፍ ቃላት ዳግም መጠቀም አይቻልም። አዲሱን ባለ 8 ካራክተሮች የይለፍ ቃልዎን ለማቀናበር  ችግሮች ካጋጠሙዎት እባክዎን አስተማሪዎን ወይም የቤተመጽሐፍት ባለሙያዎን ያነጋግሩ!

*Amharic*